# ኅብረት ችግሩና መፍትሔው

## መግቢያ
የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ በምድር ላይ የተመሰረተችው የጴንጤቆስጤ ቀን ነበር። (የሐዋርያት ሥራ 2) ይህች አዲሲቷ የክርስቶስ ኅብረተሰብ (Community)ገና እንደተመሰረተች የአባሎቿ ቁጥር 120 ብቻ ነበር። ወዲያው የአባሎቿ ቁጥር እየጨመረ መጣ። በተመሰረተችበት ቀን ብቻ አምነው የዳኑትና ወደ ኅብረተሰቡ የተቀላቀሉት ቁጥር 3000 ያህል ነበር። በዚህ ዓይነት በመስፋፋትና በማደግ የመጀመሪያው ምዕት ዓመት ከማለቁ በፊት በጊዜው ይታወቅ የነበረውን አለም በሙሉ በወንጌል መድረስ ቻለች።

ለአዲሲቷ የክርስቶስ ኅብረተሰብ (ቤተክርስቲያን)ሕይወት፣ ዕድገትና መዳበር ምክንያት የነበሩት አራት ነገሮች ሲሆኑ እነርሱም፤

ሀ. ትምህርት (Teaching)
ለ. ኅብረት (Fellowship)
ሐ. እንጀራ መቁረስ (Breaking Of Bread)
መ. ፀሎት (Prayer)ናቸው። (የሐዋርያት ሥራ 2፥42)

የመጀመሪያዊቱ ቤተክርስቲያን ሕይወት ያድግና ይዳብር የነበረው በእነዚህ አራት አቅጣጫዎች ነበር። አማኞችም ለእነዚህ አራት ነገሮች የተሰጡ ነበሩ። ከላይ በተመለከትነው ጥቅስ አማኞች ከላይ በተጠቀሱት አራት ነገሮች "... ይተጉ ነበር" ተብሎ ተጠቅሷል። አማኞች ለትምህርት፣ ለኅብረት፣ እንጀራን ለመቁረስና ለጸሎት የነበራቸው መሰጠት (Commitment) የምንመለከተው በዚህ ነው። ኅብረት (Fellowship) ከእነዚህ አማኞች ይተጉባቸው ከነበሩት አራት ነገሮች አንዱ ነው።

## ክርስቲያናዊ ኅብረት
ደህንነት ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ያስገባል። ኅብረት ደግሞ ከእግዚአብሔርና ከቤተሰቡ አባላት ጋር(ከወንድሞችና እህቶች ጋር) ያያይዝና ለጋራ ዓላማ ባንድነት ቆመን እንድንሰራ ያደርጋል። ከእኛ ማንም በሰብአዊ ባሕር የተከበበና እንደ ደሴት የሆነ የለም። እንደ ደሴት መኖር እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረበት ዓላማ ጋር አብሮ አይሄድም።

- እግዚአብሔር ቅዱሳኑን ብቸኛና ከሌላው የተቆረጡ እንዲሆኑ አይፈልግም። እያንዳንዱ ክርስቲያን ብቸኛ ደሴት ሳይሆን የአጥቢያው፣ የአካባቢው፣ የአገሩ፤ ብሎም የአህጉሩና የአለም አቀፉ ኅብረት ክፍል ነው።

- እግዚአብሔር የአጥቢያ ቤተክርስቲያንን እቅድ ሲያበጅ የእያንዳንዱ አማኝ ፍላጎት የሚሟላበትን ሁሉ አዘጋጅቶ ነው።

ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን:-

- መንፈሳዊ ምሪትን
- መንፈሳዊ ምግብን
- ወንድማማችነትንና እህትማማችነትን
- ጓደኝነትን
- መጽናናትን
- መደፋፋርና መበረታታትን ወዘተ እናገኛለን። ዕብራውያን 10፥24

እኛ አማኞች ፍፁምነትን የምናገኘው በኅብረት ውስጥ ነው። ፍላጎታችንም የሚሟላው በአንድነት ስንሆን ነው። (የሐዋርያት ሥራ 4፥32-35)

## የቃሉ ትርጉም
አንድ እንግሊዝኛ ሁለተኛ ቋንቋው የነበረ ሰው "Fellowship" (ኅብረት) ማለት ምን ማለት ነው ተብሎ ቢጠየቅ "Fellowship is fellows in the same ship" (በአንድ መርከብ ውስጥ ያሉ ሰዎች ማለት ነው) ሲል መለሰ። ይህ ሰው የሰጠው መልስ ትክክለኛው የኅብረት ትርጉም አይደለም፤ በሌላ በኩል ደግሞ መጥፎ አተረጓጎምና አመለካከትም አይሆንም። ብዙ ሰዎች ስለ ኅብረት ምንነት ብዙ የተሳሳቱ ትርጉሞች ሲሰጡ ይሰማል። ስለ ኅብረት ምንነት እውነተኛውን ትርጉም ማወቅና መረዳት ግን ትክክለኛ ኅብረት ለማድረግ ጠቃሚ ነው።

## የአማርኛ መዝገበ ቃላት ትርጉም
ከሳቴ ብርሃን ተሰማ የተባለው ያማርኛ መዝገበ ቃላት የሚከተለውን ትርጉም ይሰጠናል፤
ኅብረት፥ በባህርይ በግብር አንድ መሆን፣ መተባበር፣ በግብር አንድ አምሳል አንድ ኅብር መሆን መተባበር ኅብረት ይባላል።

የዌብስተር የተባለው የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት (Dictionary) የሚሰጠው ትርጉም

• Companionship/ ባልንጀርነት Company/ባልንጀራ Associate/ተባባሪ

• The community of interest, activity, feeling or experience, i.e, a unified body of people of equal rank sharing in common interests, goals and characteristics, etc. በአንድ ጉዳይ የተመሳሳይ ዝንባሌ፣ ተግባር፣ ወይም ልምምድ መኖር፤ እኩልነት ያላቸው ሰዎች የጋራ ዝንባሌዎቻቸውን፣ ዓላማቸውን፣ ወይም ባህሪያቸውን መከፋፈል ወዘተ. . .

• Partneship/ሽርክና/ Membership /አባልነት/

## የግሪኩ ቃል ትርጉም
በመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረት የሚለው ቃል የመጣው "ኮይኖንያ" (koinonia) ከሚለው የግሪክ ቃል ነው።
ቃሉ "ኮይኔ" (Koine)ከሚለው ቃል ጋር ዝምድና አለው። ኮይኔ ማለት "የጋራ"(common) ማለት ነው።

ኮይኔ ግሪክ ተራው የግሪክ ህዝብ ይነጋገርበት የነበረው ቋንቋ ነው። ኮይኔ ግሪክ በጊዜው ሰው ሁሉ ይነጋገርበት የነበረው ቋንቋ ስለነበር አዲስ ኪዳን የተጻፈው በኮይኔ ግሪክ ነው። በአዲስ ኪዳን "ኅብረት" (Koinonia) የሚለው ቃል ትርጉም እንደሚከተለው ነው፥

- አንድን ነገር በጋራ መካፈል፤ ወይም የጋራ የሆነ ነገር ሲኖር እንደ ሽርክና (Partnership) ተሳትፎ (Participation)

- አንድን ነገር በጋራ መከፋፈል (to share with)( በመስጠት ወይም በመቀበል አብሮ መካፈል ሊሆን ይችላል።)

በጋራ የምንካፈላቸው ነገሮች

- እግዚአብሔር
- ጌታ ኢየሱስ
- መንፈስ ቅዱስ፥ ኅብረታችን ራሱ "የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት" ተብሎ ተጠርቷል። 2ኛ ቆሮንቶስ 13፥14
- ደኅንነት 2ኛ ጴጥሮስ 2፥14
- ሌሎችም አሉ።

2.1.1. አብረን የምንከፋፈላቸው የሐዋርያት ሥራ 4፥423፣ 34፣ 35

አብረን የምንካፈላቸው ነገሮች ማቴሪያላዊ/ ቁሳቁሳዊ ብቻ አይደሉም። ደስታችንን፣ ሃዘናችንን፣ መከራችንን፣ ድላችንን፣ ድካማችንን፣ ሸክማችንን፣ ምስክርነታችንን፣ ወዘተ መከፋፈል (share ማድረግ) እንችላለን።

ስለዚህ ኅብረት እንደ ባልንጀርነት፣ ጓደኛነት፣ ማህበርተኛነት ወዘተ ጠባብ ሃሳብ አይደለም።

በአንድ ቦታ ከተከማቹ እሸዋዎች ይልቅ ባንድ ላይ ተያይዘው አብረው ወደ አንድ አቅጣጫ የሚፈሱ የውሃ ነጠብጣቦች ኅብረትን የተሻለ ይገልጹታል። ኅብረት ከውሃው ነጠብጣቦች የሚኖረው ልዩነት የሰዎች ግለሰብነት (Individuality) ሳይሻር እንዳለ መጠበቁ ላይ ነው።

ኅብረትና ግኑኝነት

የአማኞች ኅብረትና ግኑኝነት የሚጀምረው የዚህ ሁሉ መሰረቱ ከሆነው ከክርስቶስ ነው። በጋራ የምንካፈለው ሁላችንም በክርስቶስ ግንኙነት ስላለን ነው። 1ኛ ቆሮንቶስ 1፥9 እና 1ኛ ዮሐንስ 1፥3

ግንኙነት ኅብረትን ይቀድማል። ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ በመወለድ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ስንመሰርት፤ ከቀሩት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጋር የቤተሰብ ግንኙነቱ ይመሰረታል። ኅብረት ሊደረግ የሚችለው በዚህ ግንኙነት ነው።

ግንኙነት ከሌላ ኅብረት ማድረግ አይቻልም፥ ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚከለክላቸው የኅብረት አይነቶች ያሉት። 2ኛ ቆሮንቶስ 6፥14-15፣ 1ኛ/ዮሐንስ 2፥15-18፣ ያዕቆብ 4፥4

ጥያቄና መልስ

በሕይወትህም ከሁሉ የሚበልጠው ነገር ማን ወይም ምንድን ነው?
ሁለተኛውንስ ቦታ የሚይዘው ማን ወይም ምንድን ነው?
ሦስተኛውንስ?

ሰው - ማህበራዊ ፍጥረት

የመጀመሪያዎቹን ሁለት ምዕራፎች ከኦሪት ዘፍጥረት አውጥተን ስንመለከት ሰባት ጊዜ "መልካም ነው!" የሚል ቃል እናገኛለን። "መልካም አይደለም!" የሚል ቃል የተነገረው ለአዳም ብቸኛ ሆኖ መገኘት ብቻ ነበር። (ዘፍጥረት 2፥18)የአዳም ከእንስሳትና ከአጽዋት ጋር መዋል ደስታ ሊሰጠው አልቻለም። (ዘፍጥረት 2፥21-22) የሔዋን መፈጠርና ለአዳም ረዳቱ መሆን የእርሷን ከእርሱ ዝቅ ማለት (Subordinate) የሚገልጽ ሳይሆን ብቸኝነቱን ለማስወገድ መፈጠሯን የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር በቤተሰብ ጀምሮ የዳኑትን በአንድ ላይ ቤተ ክርስቲያን ብሎ እስከጠራ ድረስ ሰዎችን በኅብረት የማድረግ ሥራውን አላቋረጠም።

የሥላሴ ምሳሌ

የሰው ግንኙነት የሚያሳየው በሥላሴ አምሳል መፈጠር ምን ማለት እንደሆነ ነው።

እግዚአብሔር አንድነት (Oneness)ያለው ኅብረት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሦስት አንድነት (Tri-unity)ያለው አምላክ መሆኑን ያስተምራል።
አብ
ወልድ
መንፈስ ቅዱስ "ሥላሴ" (Trinity)እንለዋለን።
እግዚአብሔር በሦስት አንድነቱ የታወቀ ነው። በሥላሴ መካከል ግንኙነት አለ። በተናጠል (Independently) አይሰሩም። ሆኖም ሦስቱም በየተራ ግንባር ቀደም ሆነው የሚታዩበት የተለያየ የስራ ድርሻዎች አሉአቸው። ሥላሴ የግንኙነት አምላክ ስለሆነ በአምሳሉና በመልኩ የተፈጠረውም ሰው ያንን መልክ (ግንኙነት) ማንጸባረቅ ይገባዋል። ለዚህ ነው ሰው ማህበራዊ ፍጡር ሆኖ የተፈጠረው።

የኅብረት መሰረት

ግንኙነት በደም ወይም በህጋዊ እርምጃ እንደ ጉዲ ፈቻ (adoption) ባለ ሁኔታ የሚመሰረት ነው። መንፈሳዊ ግንኙነትም የልጅነትን ስልጣን ከማግኘት የተገኘ ነው። ዮሐንስ 1፥12፣ ዮሐንስ 3፥3፣ 5

የኅብረትና የግንኙነት ልዩነት

በኅብረትና በግንኙነት መካከል ልዩነት አለ። ኅብረት ከግንኙነት የበለጠ ነገር ነው። ኅብረት ሆን ብለን የምናደርገው ተሳትፎ (active partnership) ነው። ግንኙነት ግን በደም ወይም በህጋዊ ዝምድና ላይ የተመሰረተ ብቻ ነው። ቁልፉ ቃል "ሆነ ብሎ የሚደረግ" (active partnership) የሚለው ነው። (የሐዋርያት ሥራ 4፥42)የደም ዝምድናም ሆነ ህጋዊ ግንኙነት ካለን ሰዎች ጋር ኅብረት ሊኖረንም ሆነ ላይኖረን ይችላል። ለመወለድና ለመዛመድ ጥረት አላደረግንም። ኅብረት ማድረግ ግን የግል ጥረትን ይጠይቃል።



የኅብረት አስፈላጊነት

ኦክስጅን ለሰውነታችን የሚያስፈልገውን ያህል ፤ ለመንፈሳዊ ሕይወታችንም ኅብረት አስፈላጊ ነው። ዘሌዋውያን 17፥11 ደም የማይደርሰው የአካል ክፍል ይሞታል ይላል። (1ኛ ቆሮንቶስ 12፥27) ኅብረት ማድረግ ስናቋርጥ አንዳንድ ነገሮች በውስጣችን መሞት ይጀምራሉ።

ኅብረት የሚጀመረው እንዴት ነው?

የዓለም አቀፏ (የማትታየው) የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ኅብረትና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል የምንሆነው እንደዳንንና ዳግም እንደተወለድን ወዲያውኑ (Automatically) ነው።

የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ኅብረት ውስጥ የሚገባው እያንዳንዱ አማኝ ሆነ ብሎ ራሱን በኅብረቱ ውስጥ ለማስገባትና ለመሳተፍ እርምጃ ሲወስድ ነው። ቤተ ክርስቲያንም በዚህ ዓይነት ወደ ኅብረቱ የመጡትን ትቀበላለች። የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ጳውሎስን አልቀበልም ብላ ነበር። (የሐዋርያት ሥራ 9፥26-29)

ለውይይት የቀረቡ

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የየትኛው አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል ነበር?

ጳውሎስ ከዳነ በኋላ ወደ አረቢያ ሲሄድ የየትኛው አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል ነበር?

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያኖች ውስጥ በጳውሎስ ላይ የደረሰበት መጉላላት ሊደረስ ይችላልን?

ኅብረት በሁለት አቅጣጫ ሊታይ ይችላል።

ወደ ላይ ባለው አቅጣጫ (The vertical dimension)እንዲሁም ወደ ጎን ባለው አቅጣጫ(The horizontal dimension)ሊታይ ይችላል።

የላይኛው አቅጣጫ (The vertical dimension) ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ኅብረት (1ኛ ዮሐንስ 1፥3)

ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት በእግዚአብሔር ባህርይ ላይ የተመሰረተ ነው።

1ኛ ዮሐንስ 1፥5 "... እግዚአብሔር ብርሃን ነው።" ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ ከብርሃን ጋር ኅብረት ማድረግ ነው። ይህ ኅብረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ባሕርያት ይታዩበታል።

ብርሃን ባለበት ማየት ይቻላል። ከብርሃን ጋር ኅብረት ስናደርግ ጨለማውን መግፈፍና መግለጽ እንችላለን።

አንድ ጊዜ አንድ ሰው ዝናብ ሰላስቸገረው ዝናቡ እስኪያልፍለት ለመጠለል ወደ አንድ ዋሻ ይገባል። ነገር ግን እንደገመተው ዝናቡ በቶሎ አላባራም። በዚያው በዋሻ ውስጥ እንዳለ ይመሻል። በጨለማ መቀመጡን ስላልወደደውና ትንሽም ስለበረደው ባጠገቡ የነበሩትን ቅጠሎችና ጭራሮዎች ሰብስቦ እሳት አነደደ። በእሳቱ ብርሃን በዋሻው ውስጥ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ማየት ሲችል ለረዥም ሰዓታት በዋሻው ውስጥ አብሮአቸው በቆያቸው ነገሮች በጣም ተደነቀ። የሌሊት ወፍ፣ እባብ፣ ሌሎችም ብዙ ዓይነት ትላትል በዚያ ዋሻ ውስጥ ነበሩ። እነዚህን አብሮአቸው በዋሻ ውስጥ የቆያቸውን ነገሮች ማየትና ማስተዋል የቻለው ብርሃን ሲያገኝ ብቻ ነው። ብርአን ጨለማን ይገልጣል። ልክ እንደዚሁም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሲኖረን በዙሪያችን ያሉትን ጨለማ የሰወራቸውን ነገሮች ሁሉ ለማየት ችሎታ ይኖረናል።

በተጨማሪም፤

- ብርሃን ስለ ንጽህናና ስለቅድስና፤
- ከእግዚአብሔር ምሪት ስለመቀበል ፤
- ስለ እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት ያሳስባል።

" እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ የለም።"

ታድያ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት መጠበቅ የምንችለው በብርሃን ስንመላለስ ብቻ ነው። (1ኛ ዮሐንስ 1፥6-7) "ነኝ" ብለን በአፋችን በምንናገረውና ሆነን በምንገኘው ማለት በህይወት እርምጃችን መካከል ቅራኔ ሲኖር ይህ ኅብረት አይኖርም።

ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ ከዚህ የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመርመሩ

- ሮሜ 8፥29
- ሮሜ 3፥18
- ራዕይ 3፥20

ወደ ጎን (The horizontal dimension)
ኅብረትን በተመለከተ ወደ ጎን ያለው አቅጣጫ ከወንድሞችና ከእህቶች ጋር ያለንን ኅብረት የሚያመለክት ነው።
ከወንድሞችና ከእህቶች ጋር የሚኖረን ኅብረት ብዙ ነገሮችን ያካትታል።

የእርስ በእርስ ኅብረት የሚያካትታቸው ነገሮች

- በአንድነት ስብሰባ መሳተፍ - የሐዋርያት ሥራ 2፥42፣ ዕብራውያን 10፥25
- ትናንሽ ስብሰባዎችና የመጸሐፍ ቅዱስ ጥናቶች
- አንድ ለአንድ ወይም ቤተሰብ ለቤተሰብ 1ኛ ተሰሎንቄ 5፥11
- በተገኘው ዕድል የእግዚአብሔርን እውነት መከፋፈል። ምስክርነትን መከፋፈል። (sharing)
- የጌታን ራት አብሮ መውሰድ
- በፀሎት አብሮ መትጋት
- እርስ በእርስ መተማመንና መከባበር (ሮሜ 12፥10)
- በአጋፔ ፍቅር ላይ የተመሰረተ መቀባበል
- ወዘተረፈ

የኅብረት እንቅፋቶች

ኅብረትን የሚያበላሹ ብዙ እንቅፋቶች አሉ። እነዚህን ችግሮችና እንቅፋቶች ለይቶ ማወቅ መፍትሔ ለመፈለግ ይረዳል።

የኅብረት እንቅፋቶች ዝርዝር

- ኃጢአት
- በግል ብቁ ነኝ ብሎ ማሰብ
- ድንበር መከለልና መከላከል
- ራስ ወዳድነት
- የገበያተኛነት መንፈስ (Consummerism)
- መራርነት
- መከፋፈል
- ፎርማሊቲ (ሥርዓት ላይ ችክ ማለት)
- የፍቅር መቀዝቀዝ
- ልዩነትን አለመቀበል
- አለመተማመን
- ለሌላው አለመጠንቀቅ (Insensitivity)
- መፈራረድ (Judgementalism)
- ወዘተረፈ.

ኃጢአት

ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ያበላሻል፤ ያቋርጣል። ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት እንዲቋረጥ ከአደረገ የተቋረጠውን ኅብረት መልሰን ማደስ(መቀጠል) የምንችለው በንስኃ ነው። ብዙ አማኞች ከጌታ ጋር ያላቸውን ኅብረት አበላሽተውና አቋርጠው ከሌሎች አማኞች ጋር ያላቸውን ኅብረት ግን ይጠብቃሉ። እርግጥ ነው ከሰዎች ጋር ያላቸው ኅብረት አለመቋረጡ ምናልባት የተቋረጠውን ከጌታ ጋር የነበራቸውን ኅብረት መልሶ ለመቀጠል ይረዳ ይሆናል። በመሠረቱ ግን ፥ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ከአቋረጠ ከወንድሞችና እህቶችም ጋር ኅብረት ማድረግ አይወድም። ለዚህ ነው ብዙ ወንድሞችና እህቶች ከኅብረት የሚሸሹት። ሰው ለመቀረብም ሆነ እንዲቀርባቸው የማይወዱበት ምክንያት ብዙ ሊሆን ቢችልም ከምክንያቶቻቸው መካከል አንዱ ይሄ ሳይሆን አይቀርም።

የራስ ብቃት (ብቁ ነኝ ማለት)

በራሴ ብቁ ነኝ ብሎ ማሰብ የሚያስከትላቸው ችግሮች እያሌ ናቸው። አዲስ ኪዳን በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፥21-22 እንደሚያስተምረው ብቃት የምናገኘው በኅብረት ነው። ማንም ሰው ብቻውን በራሱ ብቁአይደለም። አንዳንድ አማኞች ከኅብርት ለምን እንደሚርቁ ሲጠየቁ፡ "በቤቴ አመልካለሁ" "ለብቻዬ አመልካለሁ" ሲሉ ይመልሳሉ። እንደ ዕውነቱ ከሆነ፥ በቤታችን ሆነን የምናገኛቸው በቴሌቪዥን፣ በኢንተርኔትና እና በቪዲዮ የሚቀርቡ የክርስቲያን ፕሮግራሞች ለኅብርትተጨማሪ እንጂ "ምትክ" ሊሆኑ አይችሉም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሁለትም ሦስትም ሆናችሁ በስሜ ስትሰበሰቡ እኔ በመካከላችሁ እገኛለሁ" ያለው ያ ሁለተኛና ሶስተኛ እንደኛ ያለ ሰው እንጂ በቴሌቭዥን ውስጥ የምኛየውን ምስል ወይም ትይንተ መስኮቱን (ቴሌቭዢን) ማለቱ አይደለም። " ዳዊትም ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ መልካም ነው" (መዝሙር 133) ያለው ወንድሞችን እንጂ የኤሌክትሮኒክ ሜድያውን አይደለም። የኤሌክትሮኒክ ሚድያ ተጨማሪ እንጂ ለኅብረት ምትክ ሊሆን ፈሽሞ አይገባም። ለመሆኑ በቴሌቭዥን አንድ ፕሮግራም ካየ በኋላ በውስጡ ያሉትን ውንድሞችና እህቶች እያቀፉ ሰላምታ መስጠት የሚችል አለ? ኅብረት ማድረግ ከሰው ምስል ጋር ሳይሆን በጌታ አምሳል ከተፈጠሩ ሰዎች ጋር አብሮ መሆንን ይጠይቃል።

ድንበር ሠርቶ መከላከል

"አትምጡብኝ" "አትድረሱብኝ" "ድንበሬን አትለፉ"

የኢቶሎጂ (Ethology)ጥናት ስለሰውና ስለ እንስሳት ድንበር ከላይነት ብዙ ዝርዝር ገለጻ አለው። እንሰሳትና አራዊት የራሳቸውን ጠረን ምልክት በድንበሮቻቸው ዙሪያ በማድረግ ሌላው ድንበር ጥሶ እንዳይቀርባቸው የሚከላከሉበት መንገዶች አለቸው። ሰውም ድንበር ሰርቶ ከዚህ እንዳታልፍ የሚልበት ጊዜና ወቅት አለ። እንደ ዚህ ያሉ ሁኔታዎች ለኅብረት ጎጂ ናቸው።

የግልፅነት (Glasnost) አስፈላጊነት (ያዕቆብ 5፥16)ግልጽነት ጉድለት ለኅብረት እንቅፋት ነው።
አንድ ሰው እንደናገረው አንዳንድ ሰዎች ግልጽ መሆን ስለሚቸግራቸው ሆዳቸው ታሞ ለራሴ ፀልዩልኝ ስለሚሉ ፈውስ ሳይቀበሉ ይቀራሉ።

ራስ ወዳድነት

የመጀመሪያይቱ (የሐዋርያት) ቤተክርስቲያን ከራስ ወዳድነት ነፃ ነበረች። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምናነበው፤

እርስ በእርስ መረዳዳት ነበረባት
1ኛ/ጴጥሮስ 4፥9
መተሳሰብና መደጋገፍ ነበረባት
1ኛ/ቆሮንቶስ 12፥26
እርስ በእርስ በፀሎት መደጋገፍ ነበረባት
ያዕቆብ 5፥16
የሳተውን ማቃናት ነበረባት
ያዕቆብ 5፥16
ማስተማርና መምከር ነበረባት
ቆላስያስ 3፥16
እርስ በእርስ በፍቅር ማገልገል ነበረባት
ገላትያ 5፥13

እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮች የታዩባት ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነች ቤተክርስቲያን ስለነበረች ነው። ከላይ የዘረዘርናቸው ነገሮች በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን (የሐዋርያት ሥራ 2፥42-46) በአንፆኪያ ቤተክርስቲያን (የሐዋርያት ሥራ 11፥27-30) በሜቆዶኒያ አብያተ ክርስቲያናት (2ኛ/ ቆሮንቶስ 8፥1-5) በአካያ ቤተክርስቲያናት (ሮሜ 15፥26) ይታዩ እንደነበሩ እናያለን።

ኅብረት የሚበላሸው ይህንን የመሰለ ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ ሕይወት ሲጠፋ ነው።



የገበያተኛነት መንፈስ (Consumerism)

ብዙ ሰዎች ቤተክርስቲያን የሚሄዱት ኬማርት (K-Mart) ወይም ሲ.ርስ(Seears) ለገቢያ እንደሚሄዱ ነው።
የገበያ ቦታ ገበያተኛውን ለመጥቀም በቻ የሚኖር ነው። ስለዚህ ትልቁ ጥረት በገበያተኛው ደስታ ዙሪያ ያተኮሩ ናቸው። እንደውም በአሜሪካ የንግድ ዓለም “ገቢያተኛው ንጉሥ ነው” (The Customer is the King) የሚል አባባል አለ።
ገበያተኛው ኬማርት (K-Mart) ባይስማማው ገበያውን ወደ ሲርስ (Seears) ይወስዳል። ገበያተኛው ገንዘቡን በገበያው ላይ የሚያውለው ገበያውን መቆጣጠር ሲችል ነው።

ይህንን አስተሳሰብ እንዳለ በቤተክርስቲያንና በኅብረቶች ላይ ልናመጣ ስንፈልግ ብዙ ችግር ያስከትላል። ቤተክርስቲያንም የእውነት አምድ መሆና ቀርቶ ሰዎችን ለማስደሰትና ወደ ሌ ቦታ እንዳይሄዱ ለማድረግ ማመቻመች ትጀምራለች። ሰዎችም “ገበያተኛው ንጉስ ነው” በሚል መርሆ ሲመሩ የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ ተጥሶ በዙ ኣይነት ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ።

መራርነት

መራርነት መፍትሔ ሳይፈለግለት ፀሐይ የገባበት ቁጣ ነው። የእግዚአብሔር ቃል “ተቆጡ ነገር ግን በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ።” ይላል( ኤፌሶን 4፥ 26-27)

መራርነት ለብዙ ግንኙነቶች ጠንቅ ነው።

- ጓደኝነትን ያበላሻል፤
- ትዳርን ”
- ዝምድናን ”
- የክርስቲያኖችን ኅብረት አፍርሷል።

መራርነት ለኅብረት እንዴት ጠንቅ መሆን እነሰደሚችል ለማወቅ የሚከተሉትን ጥቅሶች እናንብብ።

- መዝሙር 64፥
- ኢዮብ 7፥11
- ኢዮብ 10፥1
- ዕብራዊያን 12፥15

መከፋፈል

ከኅብረት እንቅፋቶችአንዱ መከፋፈል ነው። ዛሬ በወንጌል ስርጭት ከተሰፋፋት አብያተ ክርስቲያናትና ኅብረቶች ይልቅ የግል አጀንዳ ባላቸውና የግል አጀንዳቸውን ለመተው በማይፈቅዱ ግለሰቦች የተመሠረቱት አዳዲስ ቤተክርስቲያናትና ኅብረቶች በቁጥር ይበልጣሉ።

መከፋፈል ችግር ያባብሳል እንጂ አይቀንስም ለኅብረትም ትልቅ እንቅፋት ነው። በዚህ ድርጊት ተሳታፊ መሆን የሚያስጠይቅ መሆኑን ሐዋርያው ጳውሎስ 1ኛ/ቆሮንቶስ 3፥16-17 ገልጾታል።

ፎርማሊቲ ¬፥ ከልብ ያለሆነ በዘልማድ የሚደረጉ ነገሮችም ከኅብረት እንቅፋቶች አንዱ ነው።

የፍቅር ቅዝቃዜና ጉድለት ፥ የፍቅር ኪሳራ የክርስትና ኪሳራን ያስከትላል። በኅብረት ላይ ብቻ ሳይሆን በራሳችን ህይወት ላይ ብዙ ኪሳራና ጉዳት ያመጣል።

ልዩነትን አለመቀበል

ኅብረት ሊኖር የሚችለው ሁላችን ተጨፍልቀን አንድ ስንሆን ሳይሆን ልዩ ልዩ መሆናችን አውቀን በክርስቶስ ስንቀባበል ነው። ልዩ ልዩ መሆናችንን የድካማችን ምክንያት ሳይሆን የብርታታችን ምክንያት መሆን ይገባዋል። ነገር ግን ይህንን ባለማወቅ ልዩነቶቻችን በኅብረት ውስጥ ከሚከሰቱት ችግሮች ምክንያች አንዱ የሚሆንበት ጊዜ አለ።

አለመተማመን ፥ መተማመን የሌለበት ንግድም ይሁን ትዳር ፀንቶ አይቆምም። መተማመን የጠፋበት ኅብረትም ብዙ ችግር ያጋጥመዋል።

ለሌላው ሰው አለመጠንቀቅ ፥ ፍቅር በተግባር የሚገለፀው ለሌላው ሰው ስናስብና ስንጠነቀቅ ነው። ያ ሲጎድል ብዙ መነካከትና መቆሳሰል ስለሚመጣ ኅብረት ይተራመሳል።

- መፍረድ ፥ ፈራጅነት ሌላውን በራሳችን ሚዛን መለካት ነው። በሮሜ 14፥13 ማቴዎስ 7፥1 1ኛ/ቆሮንቶስ 4፥5 ስለዚህ ጉዳዩ የተጻውን ማንበብ ጠቃሚ ነው።

የችግሮቹ መፍትሔ

ስለችግሮቹ በምንነጋገርበት ጊዜ በዚያው ውስጥ በመጠኑም ቢሆን ስለምፍትሔው ተወያይተናል። ስለዚህ መደጋገሙ አስፈላጊ አይደለም። ከዚህ ቀጥሎ መፍትሔ ሆነው የቀረቡት ሃሳቦች ቀደም ሲል በጠቃቀስናቸው ላይ ተጨማሪ ሊሆኑ የሚችሉት ብቻ ናቸው።

በግልጽ ውይይት አለመግባባትን ማስወገድ (Clearing)

እዚህ ቦታ የምንነጋገረው ስለ ግልፅነት ብቻ አይደለም። ስለ ግልፅነት ወይም ራሽያኖች ዝነኛ ስላደረጉት ቃል “ግላስኖስት” ቀደም ሲል ተነጋግረናል። (Clearning) የምንለው ከግልፅነት የበለጠ ነገር ነው። ችግሮች ሁሉ የሚዳብሩት እውነቱን ካለመረዳት (misunderstandings) ስለሆነ ገና ችግር ከመፈጠሩ በፊትም ሆነ በኋላ በውይይት አለመግባባትን ማስወገድ መፍታት በጣም አስፈላጊ ነው። ሁሉም ሰው በዚህ ጉዳዩ ጥንቃቄ ለያደርግ ይገባዋል።
አንድ ጊዜ አንድ ዓይነሰውር ሰው በጨለማ ባትሪ እያበራ ይሄድ ነበር። ዕውር ሆኖ ባትሪ እያበራ መሄዱ ምን ጥቅም ቢሰጠው ነው ብለው የተገረሙ ሰዎች ጠጋ ብለው ምክንያቱን ጠየቁት። እርሱም “ባትሪውን አይቶ ሌላው ሰው ከእኔ ጋር ከመጋጨትና ከመላተም እንዲጠነቀቅ በዬ ነው” ሲል መለሰ። ግጭት ከመምጣቱ በፊት እያንዳንዱ ሰው ሊያደርገው የሚገባውን ጥንቃቄ ሁሉ መውሰድ አለበት።

መቀባበል ፥ ልዩ ልዩ ከመሆናችን የተነሳ ለሚያጋጥሙን ችግሮች መፍትሄው ክርስቶስ እንደተቀበልን አንዳችን ሌላውን መቀበል ነው። ሮሜ 15፥7

ኅብረት ማለት በሁሉ ነገር መስማማት አለመሆኑን መረዳት ፥ ኅብረት በሌላው ሰው ባህርይና ሃሳብ ሁሉ መስማማት ማለት አይደለም። ጳውሎስ በጴጥሮስ ባህርይና ተግባር ያልተስማማበትና የገሰፀው ጊዜ አለ። (ገላትያ 2፥11-13) ነገር ግን ኅብረታቸው አልተበላሽም።

ራስን በሌላው ሰው ቦታ አድርጎ ነገርን መመልከት ፥ ራስን በሌላ ሰው ቦታ አስቀምጦ ነገርን ማየት።

ሀ. ከመፍረድ እንድንቆጠብ ፣
ለ. ለሌላው ማሰብና መጠንቀቅ እንድንጀምር ይጠቅማል።

ስለ መብት መከራከርን ትቶ በሚያጋጥመን ያገልግሎት ዕድል መጠቀም ፥ መብት ከአንዱ ተወስዶ ለሌላው የሚሰጥ ሳይሆን ከተግባራችን ውጤት የምናገኘው (‘earn’ የሚደረግ ) ነገር ነው።

አንዱ የሌላው የአካል ክፍል መሆኑን መረዳት ፥ (1ኛ ቆሮንቶስ 12)እርስ በእርስ ብልቶች እንደሆንን ያስተምራል። ይህንን በደንብ መረዳት ሌላው በሚበረታበት ነገር ከመቅናት ይልቅ የኔ ድካም በአካሌ ክፍል (ወንድሜ ወይም እህቴ) ተሸፈነልኝ ብለን ደስ እንዲለን ያደርጋል።

ከሰዎች ፍፁምነትን አለመጠበቅ ፥ እግዚአብሔር ገና ሁላችንንም ሰርቶ አልጨረሰም። የራሳችንን ሕይወት እንኳን ስናይ ራሳችን ባደረግነው ነገር የማንስማማበትና የምንፀፀትበት ጊዜ አለ። ነገር ግን ማንኛችንም ከራሳችን ተጣልተን ኅብረት አልተውንም። እርስ በእርስም ይህንኑ በማድረግ በሰላም ማሰሪያ አንድነትንና ሕብረትን መጠበቅ አስፈላጊ ነው።

መደምደሚያ ፥ ኅብረት የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን ትተጋባቸው ከነበሩት አራት ነገሮች አንዱ ነው። ስለሆነም ወደ ጎን የምንተወው ጉዳይ አይደለም። እኛም ያኢነርሱን ምሳሌነት በመከተልና የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ ልንተጋበትና ልንጠብቀው የሚገባ ነገር ነው።

መዝሙር 133 የሚለውን እንመልከት።

ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ፥
እነሆ መልካም ነው እነሆም ያማረ ነው።
ከራስ እስከ ጢም እንደሚፈስስ፥
እስከ አሮን ጢም፥
በልብሱ መደረቢያም እንደሚወርድ ሽቱ
ነው።
በጽዮን ተራሮች እንደሚወርድ እንደ
አርሞንኤም ጠል ነው
በዚያ እግዚአብሔር በረከቱን፥
ሕይወትንም እስከዘላለም አዝዞአልና።

-



